ספריית פיג'מה

## ባርላ ባርላ በቅርጫት ውስጥ ምንድን ነው ያለው - המשך פעילויות בעקבות הסיפור




በ: ፕኒና ካዝ
ምሳሌዎች: ኦራ አያል
הוֹצָאָה: כתר
የእድሜ ክልል: ታዳጊዎች

### קְרִיאָה

**ለቤተሰባዊ ንባብ የሚሆን ጠቃሚ ምክር - መጻህፍት በሁሉም ቦታ**

ልክ እንደ ብዙ ታዳጊዎች ባርላ አያቷን – “አሁን ምን እናደርጋለን?” ብሎ ይጠይቃል። አያት በቅርጫት ውስጥ ካሉት ሰርፕራይዞች መካከል በፈለጉት ጊዜ ሊያነቡት የሚችሉበት መጽሐፍም አለ። መጽሐፍ በየትኛውም ቦታ ለመውሰድ ቀላል የሆነ ራሱን የቻለ ዓለም ነው። ዶክተሩን ስትጠብቁ፣ በመጫወቻ ስፍራው ላይ ዘና ማለት በምትፈልጉበት ጊዜ ወይም በረዥም ጉዞ ውስጥ ስትሆኑ እናንተም መፅሃፍ በቦርሳችሁ በመያዝ መዝናናት ትችላላችሁ።

### שִׂיחָה

**ውይይት - ከዘመዶች ጋር የሚኖሩ ጥሩ ጊዜያት**

ስለ ታዳጊዎች ግንኙነት ከአያቶች ወይም ከሌሎች ጉልህ የቤተሰብ አባላት ጋር መነጋገርና መጠየቅ ትችላላችሁ – ምን አንድ ላይ ማድረግ ትወዳላችሁ? ከአያቶችህ ወይም ከአጎቶችህ ጋር ብቻ የምታደርጋቸው ልዩ ነገሮች አሉ? ?በቤታቸው ውስጥ ብቻ ያሉ ልዩ እቃዎችስ አሉ

שְׁמַע

### QR ኮድ

ኮዱን ስካን በማድረግ ታሪኩን በፒጃማ ቤተ-መጽሐፍት ስብስብ ውስጥ ማዳመጥ ትችላላችሁ።

יְצִירָה

### ምናብ የወለደው ተረት

የአያቴ ታሪኮች ባርላን ያስቁታል። ምክንያቱም ምናባዊ ስለሆኑና ያልተለመዱ ነገሮችም በምናብ ውስጥ ሊከሰቱ ስለሚችሉ ነው። እንደ ‘በሾርባ ሳህን ውስጥ የወደቀው ጉማሬ’ ወይም ‘በሌሊት ብቻውን መሆንን የሚፈራ አንበሳ’ ወይም ሌላ ሐሳብን የመሰለ ታሪክ አብራችሁ ለመምጣት ሞክሩ። በአካባቢያችሁ ካለ ነገር ጀምሮ ታሪኩ የት እንደሚደርስ ማየት ትችላላችሁ።

מִשְׂחָק

### ... አያት ኬክ ጋግራለች

አያት ገንፎ አብስላለች’ የሚለውን የጣት ጨዋታ ታውቃላችሁ? ተመሳሳይ ጨዋታ መጫወት ትችላላችሁ – ጣቶቻችሁን ወደ ውስጥ በማጣጠፍ አውራ ጣትን አውጡ፤ እነሆ – ‘ቀንድ አውጣ’ ኖራችሁ ማለት ነው። የሕፃኑ መዳፍ በትንሽ ጎድጓዳ ሳህን ውስጥ ሊኖር ይችላል፡- ከዚያ እናንተ እንዲህ ትላላችሁ -“አያትና ባርላ ኬክ ጋገሩ፣ ዱቄት ጨመሩ፣ ስኳር ጨምሩ፣ እንቁላል ጨምረዋል...” ከእያንዳንዱ ምርት ጋር የህፃኑን መዳፍ በአውራ ጣት መንካት። ሚናዎችን መቀያየርም ይቻላል።

הַשְׁרָאָה

**ፒንተረስት**

ለተጨማሪ ሀሳቦችና አስገራሚ ነገሮች የፒጃማ ቤተ መፃህፍት ፒንተረስትን ጎብኙ

עוד פעילויות באתר ספריית פיג'מה www.pjisrael.org